ቅሬታዎችን የቀነሰው ዘመናዊ አሠራር
ገጽ 3

ደንበኞች ሲያሚሉ የሚገባቸው ጉዳዮች
ገጽ 4

About auditing
ገጽ 7





# ገቢያችን ህልውናችን

14ኛ ዓመት | ቁጥር 164 | በነፃ የሚታደል





## የአዲስ ዓመት ምኞት!

**አዲሱ ዓመት (2016 ዓ.ም.) ግብር ከፋዮች በተሰማሩበት መስክ አትርፈው ግብራቸውን በታማኝነት የሚከፍሉበት፤ ሁሉም ኅብረተ-ሰብ ኮንትሮባንድን ተፀይፎ ለሕጋዊ ንግድ ጠበቃ የሚሆንበት፤ የገቢ ሰብሳቢ ሠራተኞችም ሥራቸውን በታማኝነት እና በቅንነት የሚያከናውኑበት እንዲሆን እንመኛለን!**

## ከአፍሪካ ሊደር ሺፕ መጽሔት ተሸላሚዎች መካከል

የአፍሪካ ሊደርሺፕ መጽሔት የሚገኘው እንግሊዝ ሲሆን የሚታተመውም አፍሪካን ሊደርሺፕ በተሰኘ ድርጅት ነው፡፡ ድርጅቱ የተቋቋመበት ዓላማም ምርጥ የአፍሪካ መሪዎችን በመለየት ዕውቅና መስጠት ነው፡፡ እ.ኤ.አ በ2008 ዓ.ም ከጀመረ ጊዚያት አንስቶ ለበርከታ አፍሪካ መሪዎች ዕውቅና ሰጥቷል፡፡ ከነዚህም መካከል በኬንያ የኬሲቢ ባንክ ዳይሬክተር አናስቲኪያ ኮማቲ ፣ የታንዛንያ የሌክ አይል ግሩፕ ሥራ አስኪያጅ አሊ ኤድሃ እና የሞሪሺየስ የፋይናንስ ዕቅድና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር ሬግናነዴን ፓዳይቻ ይገኙበታል፡፡ በቅርቡ ደግሞ ለጉምሩክ ኮሚሽነር አቶ ደበሌ ቃበታም በተመሳሳይ ሁኔታ እውቅናውን ሰጥ ቷ ል፡፡



ከመጽሔቱ ተሸላሚዎች አንዱ ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ፤

# የ180 ት/ቤቶች ጀግና


ለመጨረሻ ውድድር የቀረቡ ተማሪዎች፤



ከአዲስ አበባ 777 ኪሎ ሜትር በምትርቀው አሶሳ ከተማ ከሚገኙት የግል እና የመንግሥት ት/ቤቶች መካከል አሶሳ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አንዱ ነው፡፡ በዚህ ት/ቤት ሺዎች የሚማሩ ሲሆን የ2016 ዓ.ም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መልቀቂያን (ማትሪክን) የሚፈተነው ናሆም ሹማ ከሺዎቹ መካከል ነው፡፡

ናሆም ከዚህ በፊት በኑሐማ አፀደ-ሕጻናትና አንደኛ ደረጃ ት/ቤት እስከ ስምንተኛ ክፍል ሲማር አብዛኛውን አንድ አንደኛ እየወጣ ያለፈ ሲሆን ሁለተኛ እና ሦስተኛ ደረጃን ያገኘባቸው ክፍሎች ጥቂት ናቸው፡ ፡ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከገባ በኋላ ግን አንደኛነቱን ካለማስቀማቱም በላይ ከአጠቃላይ ክፍሎች ሁሉ አንደኛ እየወጣ ነው 12ኛ ክፍል የደረሰው፡፡

‹‹ብዙ ጊዜ ከቤት ባልወጣም ሳላበዛው እንደማንኛውም ልጅ ተጫውቼ ነው ያደግሁት›› የሚለው ናሆም ጊዜውን ለጨዋታ እና ለትምህርቱ ብቻ ሳይሆን በጎን ለመጣለት ሌላም ዕድል አመቻችቶ ውጤት አግኝቶበታል፡፡

የገቢዎች ሚኒስቴር ታክስ ከፋዮች ትምህርት ዳይሬክቶሬት ከሚሠራቸው ስለታክስ ግንዛቤን መስጠት መካከል በት/ቤቶች ውስጥ የታክስ ክበባትን በማቋቋም በነርሱ በኩል ለተማሪዎች እውቀትን ማስረፅ ነው፡፡

በዚህ ረገድ በሚኒስቴሩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በኩል ጭምር በት/ቤቶች እየተሠሩ ከሚገኙት አንዱ በተማሪዎች መካከል በግብር እና በጉምሩክ ጉዳዮች ላይ የሚካሔድ የጥያቄና መልስ ውድድር ነው፡፡ በዚህ መሠረት ዘንድሮ በዘጠኝ ምድብ ተከፍለው በመላ ሀገራችን ከሚገኙት መካከል 180 ት/ቤቶች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ዘጠኙ ምድቦች የየምድባቸውን አሸናፊ ከመለየታቸው አስቀድሞ ለየምድቡ የሚያልፉትን የለዩት ከእያንዳንዱ ት/ቤት በመነሳት ነው፡፡

ይህን መንገድ ከተሳተፉት መካከል ከላይ ያስተዋወቅናችሁ ተማሪ ናሆም ሹማ ይገኝበታል፡፡ ናሆም ውድድሩን የጀመረው አሶሳ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በትምህርት ውጤታቸው ከላቁት ውስጥ ከተመረጡት ስምንት ተማሪዎች ጋር ነበር፡፡ በዚህ ውድድር ሁለት ተማሪዎች ሲያልፉ ናሆም አምኛ ወጥቷል፡፡

ቀጣዩ ውድድር በቤንሻንጉል ክልል ት/ቤታቸውን ከወከሉ የአራት ት/ቤቶች ጋር ስለነበር ይህንንም ሁለት ተማሪዎች ሲያሸንፉ ናሆም አንደኛነቱን አልለቀቀም፤ የመጽሐፍ ሽልማትም ተበርክቶለታል፡፡


ሦስተኛው ዙር ውድድር ከዘጠኙ ምድቦች አንዱ በነበረው በባህርዳር የተካሔደው ሲሆን አንድ ተወዳዳሪ ብቻ ወደ ቀጣዩ የመጨረሻ ዙር በሚያልፍበት ውድድር ልማደኛው ናሆም አንደኛነቱን ሳያስነጥቅ የታብሌት ተሸላሚ ሆነ፡፡

የመጨረሻው ውድድር አዲስ አበባ ላይ ሰኔ 24/2015 ዓ.ም. በስካይ ላይት ሆቴል ሲሆን እንደ ናሆም የየምድቦቻቸውን ውድድር በአንደኛነት በተወጡ ናሆምን ጨምሮ በዘጠኝ ተማሪዎች መካከል የተካሔደ ነው፡፡ በዚህም ናሆም ስምንቱን የየምድቦቻቸው አንደኞችን አሸንፎ ከውድድሩ የክብር እንግዶች ከገቢዎች ሚኒስትር ወ/ሮ ዓይናለም ንጉሴ እና ከኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ እጅ የኮር አይ 7 ላፕቶፕ ሽልማቱን ተቀብሏል፡፡

በውድድሩ ናሆምን ተከትለው አቤል ታዬ ከአዋሽ ነሚልሰን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና ሙና አብዱላሂ ከሐረር ጀግኖች መታሰቢያ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

**የ180 ት/ቤቶች... ወደ ገጽ 2 ዞሯል**

# ርዕሰ አንቀጽ



## የሕሊና ዘመን

መላው ግብር ከፋዮቻችን፤ ከሁሉ በፊት እንኳን ከ2015 ወደ 2016 ዓ.ም. አዲስ ዓመት አደረሳችሁ! ዘመን ሲለወጥ የመጀመሪያው ባይሆንም ሁሌ አዲስ የሚሆነው ቁምነገር ሲሠራበት ነው፡፡ ቁምነገር ለመሥራት ደግሞ ለራስም፣ ለሌሎችም ሆነ ከምንም በላይ ለሕሊና ቃል መግባት ይገባል፡፡

ባለፈውም ሆነ ከዚያ በፊት በነበሩ ዓመታት በግል ሕይወትም ሆነ በሥራ ላይ ድክመት ላይ የተገኘ ሰው ዘመን ሲለወጥ ከነድክመቱ መሻገር የለበትም፡፡ ባለፉት ዓመታት በሕገ-ወጥ ንግድ ተሰማርቶ የነበረ ሰው ከሕግ አስከባሪዎች ጋር የዐይጥ እና የድመት አባሮሹ እንደማያዋጣው ተረድቶ ወደ ታማኝነት መመለስ ይገባዋል፡፡ በግብር ማጭበርበር፣ በታክስ ስወራ እና በሕገ-ወጥ ደረሰኝ ሲገበያይ የኖረ ካለ ያን ልምድ ትቶ ለራሱም፣ ለመንግሥትም ሆነ ለፈጣሪም የታማኝነት እድሳት ማድረግ አለበት፡፡

ኮንትሮባንድ ሕጋዊ የንግድ እንቅስቃሴን ከማዛባቱ አልፎ በወገን ጤና ላይ ጉዳት እንደሚያደርስ እያወቀ በዚህ ተሰማርቶ ያለፉትን ዓመታት ያልተገባ ትርፍ ያካበተ ሰው አለና ያለፈው ዘመን በቁጥር ብቻ ሳይሆን በምግባርም እንዲለወጥ በመታረም ራስን መለወጥ ይገባዋል፡፡

ብዙ ጊዜ ዘመን ሲለወጥ የሲጋራ፣ የመጠጥ፣ የጫት እና የሌላም ሱስ ያለባቸው ለማቆም መስከረም 1 ላይ ቃል ይገቡና አብዛኞቹ በቃላቸው ሲገኙ እናውቃለን፡፡ ከላይ በጠቀስናቸው ሕገ-ወጥ ተግባራት ላይ ተዘፍቀው ሀገር እና ሕዝብ እየጎዱ ያሉ ወገኖችም ልክ እንደሱሰኞቹ ተጸጽተው የበደሉትን ሕዝብ ባደሱት ታማኝነት መካስ አለባቸው፡፡

ይህ መታደስ ግዴታቸውን ለማይወጡ ግብር ከፋዮች እና ለኮንትሮባንዲስቶች ብቻ ሳይሆን ለታማኞቹም ያስፈልጋል፡፡ ታማኝ ሰዎች ያልታመኑትን መጀመሪያ በምክር፤ አልሆን ሲላቸው ደግሞ እርምጃ ለሚወስድ አካል በመጠቆም ከሕገ-ወጥ ድርጊታቸው እንዲታቀቡ ማስደረግ አንዱ የዘመን ለውጥ ቃል መግቢያ ነው፡፡

እንዲህ የምንለው ግብር ከፋዮችን ብቻ ሳይሆን የገቢ ሰብሳቢ ተቋማት ሠራተኞችንም ጭምር በመሆኑ ሁላችንም በየተሰማራንበት ተግባር ታምነን የጋራ ለሆነችው ሀገር እንደዘመኑ አዲስነት አዲስ ታሪክ ማስመዝገብ ስለሚገባ ነው፡፡



የአጠቃላይ አሸናፊው ናሆም ሹማ፤

## የ180 ት/ቤቶች...

ከገጽ 1 የዞረ

ሁለተኛ እና ሦስተኛ በመውጣት የኮር አይ 5 እና 3 ላፕቶፖች ተሸላሚ ሆነዋል፡፡ ከአራተኛ እስከ ዘጠነኛ የወጡት ተወዳዳሪዎች ደግሞ የታብሌት ሽልማታቸውን ተቀብለዋል፡፡ ከተወዳዳሪዎቹ በተጨማሪ ተወዳዳሪዎቹን ለውጤት ያበቋቸው ዘጠኝ መምህራን እንዲሁም ዘጠኙ ተወዳዳሪዎች የመጡባቸው ት/ቤቶች ርዕሰ-መምህራን የገንዘብ ሽልማት አግኝተዋል፡፡

በጉምሩክ ኮሚሽነር የተከፈተው የጥያቄና መልስ ውድድሩ መርሐ-ግብር በገቢዎች ሚኒስትር ንግግር ሲዘጋ ሚኒስትሯ፤ ዘጠኙም ተወዳዳሪዎች የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን እስኪያጠናቅቁ ሚኒስቴሩ እና ኮሚሽኑ ሀብት በማፈላለግ የትምህርት ወጪያቸውን ለመቻል ቃል ገብተዋል፡፡

ገቢያችን ህልውናችን፤ በገቢዎች ሚኒስቴር የኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት፡- አቶ እስክንድር መርሐጽድቅ ሰብሳቢ
አቶ ፀጥአርጋቸው ንጋቱ አባል

ዋና አዘጋጅ፡- እስክንድር መርሐጽድቅ
አዘጋጅ፡- ሺመልስ ሲሳይ
ሰሎሞን ወርቁ
እታገኝ አቦሰጥ

ጸሐፊና ሌይአውት ዲዛይነር፡- ብርሃኔ ደመቀ
ፎቶግራፈር፡- ክፍሌ አዳፍሬ፣ እስካለም ሰፊው እና የትናየት እንዳያፍሩ

አድራሻ፡- ስልክ 011-6-62-98-17 ፋክስ 011-6-67-39-14
ፖ.ሣ.ቁ 2559 ዌብሳይት www.mor.gov.et
ኢሜል ethioerca@Gmail.com
ፌስቡክ Ministry of revenues of Ethiopia
ለታክስ እና ለጉምሩክ ጉዳዮች መረጃ ነጻ ስልክ 8199




## ቢሊየን ብሮች የወጡባቸው ማኅበራዊ ኃላፊነቶች

ከሃገራችን በርካታ በጎ ልማዶች መካከል የበጎ ፍቃድ ተግባር አንዱ ሲሆን በዚህ በኩል ግለ-ሰቦች እና የግል ድርጅቶች በስፋት ይታወቃሉ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን መንግሥት ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እንቅስቃሴ የጀመረ ሲሆን ከዕለት ፍጆታ እስከ ቤት ሠርቶ መስጠት ድረስ በስፋት ተሰማርቶ ይገኛል፡፡

ከዚህ አኳያ የገቢዎች ሚኒስቴር እና ጉምሩክ ኮሚሽን ከተሰጣቸው ሃገራዊ ኃላፊነት እና ተግባር በተጓዳኝ መንግሥትን እና ሕዝብን ሊያቀራርቡ የሚችሉ በርካታ የበጎ አድራጎት ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

ተቋማቱ ባለፉት አምስት ዓመታት ከ8.2 ቢሊየን ብር በላይ በሆነ ወጪ ለ210 አቅመ-ደካሞች የቤት ዕድሳት፣ ለበርካታ ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ እና በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሰራሽ ችግሮች ጉዳት ለደረሰባቸው የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች እገዛ አድርጓል፡፡ እንዲሁም በአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብር ሠራተኞቹ ብዙ ሺ ችግኞችን ተክለዋል፡፡



እነዚህ ተቋማት ባደረጉት የበጎ ፍቃድ ተግባር በመንግሥት ላይ ጽኑ ዕምነት እንዲኖራቸው አድርጓል፤ በመንግሥት ደረጃ የሚከናወኑ ማናቸውም ተግባራት ላይ የባለቤትነት ስሜትን አዳብረዋል፤ መንግሥት እና ህዝብ እንዲቀራረቡም ሚናቸውን ተጫውተዋል፡፡

ይህ ተግባር በቀጣይ ጊዜያትም በተፈጥሮ እና በሰው ሰራሽ አደጋዎች ለተለያዩ ችግሮች ለተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች ባለፈው ከተደረገው በተጠናከረ ሁኔታ ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን ይወጣሉ፡፡

## የዕቅዱን 184 በመቶ ያሳካው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ከአዲስ አበባ 761 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የምትገኘው መቀሌ የገቢዎች ሚኒስቴር ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከሚገኙ መ/ቤቶች አንዷ ነች፡፡ ቅ/ጽ/ቤቱ በፌዴራል እና በትግራይ ክልል መንግሥታት የተከሰተውን አለመግባባት ተከትሎ ለተወሰኑ ጊዜያት አገልግሎቱ ተቋርጦ ቆይቷል፡፡

በሁለቱ አካላት መካከል በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ በተደረገው ስምምነት መሠረት ሁሉም የመንግሥት መ/ቤቶች ሥራቸውን ሲጀምሩ የገቢዎች ሚኒስቴር መቀሌ ቅርንጫፍ ቅርንጫፍ ጽ/ቤትም የ2015 በጀት ዓመት ሥራውን ጀምሮ ነበር፡፡

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በበጀት ዓመቱ 403 ሚሊዮን ብር እንዲሰብሰብ ታቅዶለት የሰበሰበው 743 ሚሊየን ብር መሆኑን የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ወ/ሮ ጸሐይ አማረ ገልጸዋል፡፡ በዚህም መሰረት የዕቅዱ 184 በመቶ ተሳክቷል፡፡

ይህ ስኬት ይመዝገብ እንጂ በክልሉ የነበሩት አለመረጋጋቶች፣ የብዙ ግብር ከፋዮች ንብረት መውደም፣ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሠራተኞች ለረጅም ጊዚያት ደመወዝ ባለመከፈሉ ውዝፍ የቤት ኪራይ መበራከት እና መሰል ችግሮች ከዚህም በላይ ገቢ እንዳይሰበሰብ አድርጓል፡፡

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በ2016 በጀት ዓመት ሦስት ቢሊየን ብር ለመሰብሰብ ዕቅድ ተይዞለት በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

# እንግዳችን

አዘጋጅ፡- ሺመልስ ሲሳይ

# ቅሬታዎችን የቀነሰው ዘመናዊ አሠራር

የጉምሩክ ኮሚሽን ካሉት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አንዱ የሞጆ ጉምሩክ ነው፡፡ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን የተለያዩ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓቶች እና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች አስመልክቶ ሥራ አስኪያጁ አቶ ጌቱ ዓለሙ ገለጻ አድርገውልናል፡፡

በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የሚካሄደው የቁጥጥር ስርዓት ምን ይመስላል?

ዕቃዎች ለነጻ ዝውውር ከመለቀቃቸው በፊት ሙሉ የኢንተለጀንስ አቅማችንን ተጠቅመን ጠንካራ የቁጥጥር ሥራ እንሠራለን፡፡ ለምሳሌ አንድ ተሽከርካሪ ከጋላፊ ተነስቶ መቼ ሞጆ መድረስ እንዳለበት የተቀመጠለት የጊዜ ገደብ አለ፡፡

ተሽከርካሪው ሞጆ ከደረሰ በኋላም እስካሁን ያለውን ሁኔታ መረጃ ለማጣራት አካላዊ እና የኦንላይን ፍተሻ ይደረጋል፡፡ በአካላዊ ፍተሻው አጠራጣሪ ነገሮች ካሉ ወደ ሕግ ማስከበር ተልኮ እሽጉ ትክክል መሆን አለመሆኑ፣ ብሎኖቹ ያልተፈቱ መሆናቸው እና በሮቹ በተነሱበት ሁኔታ እዚህ መድረሳቸው ይረጋገጣል፡፡ በተደረገው ክትትልም ተሽከርካሪው ላይ ጉድለት ከተገኘበት እና አሽከርካሪው ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ በሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

ዕቃዎች በስጋት ደረጃቸው በሦስት ይከፈላሉ፡፡ የመጀመሪያው፤ ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ያላቸው ሲሆን የዕቃዎቹ ባለቤት ታማኝ ግብር ከፋዮች፣ አምራቾች፣ ላኪዎች እና ፕሮጀክቶች የመሳሰሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ዕቃዎች ከነጋዴ ዕቃዎች ጋር ውድድር ውስጥ ስለማይገቡ መጠነኛ ፍተሻ ከተደረገ በኋላ ወዲያውኑ ይለቀቃሉ፡፡

ሁለተኛው መካከለኛ የስጋት ደረጃ ያላቸው ዕቃዎች ሲሆኑ እነዚህ ዕቃዎች የሰነድ ምርመራ ከተደረገላቸው በኋላ የሚለቀቁ፤ የሚመረመረው የሰነድ አይነትም የተጨማሪ እሴት ታክስን እና የመሳሰሉትን የሚያካትት ነው፡፡

ሦስተኛው የዕቃ አይነት ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ያላቸው ሲሆኑ እነዚህ ዕቃዎች በክፍት ወይም በዝግ መጋዘን ጥልቅ ፍተሻ ይደረግባቸዋል፡፡ በፍተሻውም የዕቃው ስሪት፣ ዓይነት እና ሌሎችም ምርመራ ይደረግባቸዋል፡፡

ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ያላቸው ዕቃዎች የፍተሻ ስርዓታቸው ጠበቅ አለማለቱ ሕገ-ወጥነትን አያስፋፋም?

እነዚህ ዕቃዎች ሙሉ በሙሉ በፍተሻ ስርዓቱ አያልፉም ማለት አይደለም፡፡ የእነዚህን ዕቃዎች ባለቤቶች ታማኝነት ለማረጋገጥ በየጊዜው ሙያዊ የኦዲት ሥራ ይደረጋል፡፡ በተደረገው የኦዲት ሥራ ታማኝነታቸውን ካጓደሉ በመመሪያው መሠረት ሕጋዊ እርምጃ ይወሰድባቸዋል፡፡

የሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት መልቲ ሞዳል የትራንዚት አገልግሎቱን ቀልጣፋ ለማድረግ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያላችሁ ቅንጅት ምን ይመስላል?

የመልቲ ሞዳል የትራንዚት አገልግሎትን የደንበኞን ፍላጎት ማዕከል አድርጎ ለመስጠት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሠራን ነው፡፡

ከሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ጋር በቅንጅት ከሚሠሩ አካላት መካከል ትራንስፖርት ሚኒስቴር፣ ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ ፌዴራል ፖሊስ፣ መድሃኒት እና ምግብ ቁጥጥር ባለስልጣን፣ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክ አገልግሎት እና ሌሎቹም ይገኙበታል፡፡ እነዚህ አካላት በሞጆ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የራሳቸው ተቆጣጣሪ አካላትን በመመደብ ሥራቸውን በመሥራት ላይ ይገኛሉ፡፡

ከ2010 ዓ.ም. ጀምሮ የመጣውን ለውጥ ተከትሎ በሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ያለው አፈጻጸም ምን ይመስላል?

መጀመሪያው ያከናወንነው አገልግሎት አሰጣጣችንን ዘመናዊ ማድረግ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በተቋማችን የሚሰጠው አገልግሎት ኦንላይን በመሆኑ ከእጅ ንክኪ ነጻ ተደርጓል፡፡ ይህንን በማድረጋችንም ካሁን ቀደም በቅርንጫፍ ጽ/ቤታችን ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር ተያይዞ ይነሱ የነበሩ ቅሬታዎችን ማስቀረት ተችሏል፡፡

በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቅም በኩል በአሽከርካሪዎች ላይ ጂ.ፒ.ኤስ በመግጠም አስመጪዎች ንብረታቸውን በቅርበት እንዲከታተሉ ተደርጓል፡፡ ባለንብረቶች ይህንን ቴክኖሎጂ ተጠቅመው በኦንላይን በመከታተል መዘግየት ሲገጥማቸው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ እንደሚችሉም ተደርጓል፡፡

ለሠራተኞቻችን ምቹ የሥራ አካባቢን ለመፍጠር ሌላው የጠሠራው ተግባር ተቋሙን እንደ አዲስ የማደራጀት ሥራ ነው፡፡ ካሁን ቀደም ቢሯችን በርካታ የተዝረከረኩ ነገሮች ስለነበሩት ሠራተኞች ምቾትን እንዳያገኙ አድርጓቸው የነበረ ሲሆን አሁን ግን ቢሮው ተስተካክሎ ያማረ ሆኗል፡፡


ተጨማሪ የሚገልጹት ነገር ካለ?

በዘመነ-ሉላዊነት /Globalization/ ዓለም አንድ መንደር ከሆነች ሰንብታለች፡፡ በዚህ ጥብቅ የትስስር መንደር ውስጥ መቆየት የሚቻለው በሁሉም ዘርፍ ከዘመኑ ጋር የሚሄድ አገልግሎት መስጠት ሲቻል ብቻ ነው፡፡

ምንም እንኳን በሃገራችን ቴክኖሎጂን መጠቀም ላይ ውስንነቶች ቢስተዋሉም በዓለም ዓቀፍ ገበያ ላይ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቅረብ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም አማራጭ የለውም፡፡ ስለሆነም ባለሃብቶች ይህንን አሠራር ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል ደግሞ በተሰማራበት የሥራ መስክ ለቀልጣፋ እና ለውጤታማ ሥራ መትጋት ይጠበቅበታል፡፡



የሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ አቶ ጌቱ ዓለሙ፤



የሞጆ ደረቅ ወደብ፤

## ማረሚያ

ባለፈው (በቁጥር 163) ዕትም በሚኒስቴራችን የባህርዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤትን አስመልክቶ በሠራነው ቃለ-መጠይቅ የሥራ አስኪያጁን የአቶ ካሣሁን ደመመን ፎቶ ካስቀመጥን በኋላ የፎቶ መግለጫው (ካፕሽን) ስር የርሳቸውን ስም አስፍረን ‹‹የኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ›› ማለታችን ስህተት ስለሆነ ‹‹የባህርዳር ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ›› በሚለው እንዲስተካከል ከይቅር ጋር እንጠይቃለን፡፡

# ለግንዛቤዎ

አዘጋጅ:- ሰሎሞን ወርቁ

# ደንበኞች ሲያሟሉ የሚገባቸው ጉዳዮች

(ካለፈው ዕትም የቀጠለ)

**ከንግድ አሠራር ጋር በተያያዘ ምዝገባና የምዝገባ ለውጦችን የማሳወቅ አገልግሎት**

**አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች**

- በአግባቡ ተሞልቶ የቀረበ ለውጥ ማሳወቅያ ቅጽ፤
- በታስክ ከፋይ የምዝገባ ለውጥ ሲደረግ ለውጡ በተደረገ በ30 ቀናት ውስጥ ማሳወቅ፤

**አገልግሎቱ የሚሰትበት የስራ ክፍል**

- የታክስ ከፋዮች ምዝገባና አገልግሎት የስራ ሂደት/ቡድን

አገልግሎቱየሚሰትበት ሁኔታ

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ስረዛ**

**አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች**

- የምዝገባ ስረዛ ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ፤
- የኦዲት የሚያስፈልጉ የሂሳብ መዝገብና ደጋፊ ማስረጃዎች፤
- በተሰማራበት ንግድ ፈቃድ ምንም ያልሠራ ከሆነ ስላለመስራቱ ከሚመለከተው የታክስ ባለስልጣን የሥራ ክፍል እና ከሦስተኛ

  ወገን ማረጋገጫ ማቅረብ፤
- ከታክስ እዳ ነጻ ክሊራንስ፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**አገልግሎቱ የሚሰትበት የስራ ክፍል**

- የታክስ ከፋዮች ምዝገባና አገልግሎት የስራ ሂደት/ቡድን

**አገልግሎቱየሚሰትበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ አገልግሎት**

**ሀ) የግዴታ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ አገልግሎት**

**አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች**

- በ12 ወራት ውስጥ ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች ጠቅላላ ዋጋ ከብር አንድ ሚሊዮን የሚበልጥ መሆኑን ማስረጃ ማቅረብ፤
- ቋሚ የመኖሪያ፣ የማረፊያ ወይም የንግድ ቦታ ማስረጃ፤
- የባንክ ሂሣብ ደብተር፤
- የታክስ ከፋይነት ምዝገባ የምስክር ወረቀት፤
- የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት የስራ ክፍል**

- የታክስ ከፋዮች ምዝገባና አገልግሎት የስራ ሂደት/ቡድን

**አገልግሎቱየሚሰትበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**ለ) በፈቃደኝነት ለተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ**

**አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች**

- 75% ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመዘገቡ ጋር መሆኑን ማስረጃ ማቅረብ፤
- ቋሚ የመኖሪያ፣ የማረፊያ ወይም የንግድ ቦታ፣ ተቀባይነት ያገኘ የሂሳብ መዝገብ፤
- የባንክ ሂሣብ ደብተር፤
- የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት፤
- የንግድ ሥራ ፈቃድ ዋና ምዝገባ የንግዴ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት የስራ ክፍል**

- የታክስ ከፋዮች ምዝገባና አገልግሎት የስራ ሂደት/ቡድን

**አገልግሎቱየሚሰትበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**ሐ) የተናጥል ለተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ**

**አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች**

- ቋሚ የመኖሪያ፣ የማረፊያ ወይም የንግድ ቦታ፤
- ራሱን የቻለ የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መዘርጋት፤
- ለቅርንጫፍ ንኡስ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ማውጣት፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት የስራ ክፍል**

- የታክስ ከፋዮች ምዝገባና አገልግሎት የስራ ሂደት/ቡድን

**አገልግሎቱ የሚሰትበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**መ) ቋሚ የተጨማሪ እሴት ታክስ ስረዛ**

**አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች**

- ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ያለው የሶስት ዓመት ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ባሉት 12 ወራት ውስጥ የሚያከናውናቸው ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች ጠቅላላ ዋጋ ከብር አንድ ሚሊዮን በታች መሆኑን ማረጋገጥ፤
- ታክሱ የሚከፈልበትን ግብይት ከተቋረጠበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ ምዝገባው እንዲሰረዝ ማመልከቻ ማቅረብ፤
- ያለበትን የታክስ ዕዳ ክፍያ አጠናቅቆ መክፈል፤
- የተሰጠውን የምዝገባ የምስክር ወረቀት መመለስ፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት የስራ ክፍል**

- የታክስ ከፋዮች ምዝገባና አገልግሎት የስራ ሂደት/ቡድን

**አገልግሎቱየሚሰትበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**የኤክሳይዝ ታክስ ማመልከቻ መቀበል፣ ምዝገባ ማካሄድ፣ መስክ ጉብኝት ማድረገና ፈቃድ መስጠት**

**አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች**

- የጸና የንግድ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብ፤
- የአመራረት ሂደቶችን የሚገልጽ ማስረጃ፤
- የንግድ ስራው የሚያካሂድበት ሁኔታዎች የሚገልፅ የጽሁፍ ማስረጃ፤
- የማምረቻ ህንጻ ፕላን፣ ክፍሎች / ቦታዎች የሚገኙበትን ሁኔታና አካባቢውን የሚገልጽ ፕላን ኮፒ የማምረቻ መሳሪያዎች ማስረጃዎች እና መግለጫዎች፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት የስራ ክፍል**

- የታክስ ከፋዮች ምዝገባና አገልግሎት የስራ ሂደት/ቡድን

**ለአገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በፋብሪካው በአካል በመገኘት፣ በመስክ ጉብኝት በማረጋገጥ

**የክፍያ ማስረጃ የምስክር ወረቀት (የክሊራንስ) አገልግሎት**

**ሀ) ዓመታዊ የንግድ ስራ ፈቃድ ለማደስ፣ በጨረታ ለመሳተፍ እና ከባንክ ብድር ለማግኘት የሚጠየቅ የምስክር ወረቀት (ክሊራንስ) አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች**

- ማንነትን የሚገልጽ መታወቂያ፤ ወኪል ከሆነ ህጋዊ ውክልና ማስረጃ ኦርጂናል እና ኮፒ፤
- የዘመኑን ግብር/ታክስ አስታውቆ መክፈሉን ማረጋገጫ፤
- የክፍያ ጊዜ ስምምነት ከተገባ ይህንን የሚገልጽ ማስረጃ፤
- የታክስ ውሳኔ መስታወቂያ ከተሰጠውና ያልተከፈለ የታክስ ዕዳ ካለ የታክስ ዕዳ አጠቃላይ መክፈል ወይም ከእዳው ጋር ተመጣጣኝ የባንክ ዋስትና ማቅረብ (የባንክ ብድር)፤
- በታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ/አቤቱታ ቀርቦ በመታየት ላይ የሚገኝ ከሆነ ቅሬታ/አቤቱታ መቅረቡን የሚያመለክት ማስረጃ፤
- የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ መግዛቱና ዓመታዊ ዕድሳት ስለመደረጉ ማረጋገጫ፤
- ግብር ከፋዩ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር የደረሰበት ከሆነ ይህንን የሚያረጋገጥ ማስረጃ (በልዩ ሁኔታ የክሊራንስ አገልግሎት)፤
- የግብር እፍይታ /የቀረጥ ነፃ መብት ያለ ከሆነ ይህንኑ የሚገልፅ ማስረጃ፤
- በተሰማራበት ንግዴ ፈቃድ ምንም ያልሠራ ከሆነ ስለመስራቱ ከሚመለከተው የታክስ ባለስልጣኑ የሥራ ክፍል እና ከሦስተኛ ወገን ማረጋገጫ ማቅረብ፤
- የኮንስትራክሽን ማሽነሪ በተመለከተ የፈቃድ ማደሻና ቦል ለማስድረግ በተለያየ ምክንያት ያለመስራቱን ለታክስ ባለስልጣኑ በህጉ በተፈቀደው ጊዜ ውስጥ ያስታወቀ መሆኑን፤
- በትራንስፖርት ዘርፍ የተሰማራ ታክስ ከፋይ በታክስ ማስታወቂያ ጊዜ ታክስ ያልከፈለው የተሸከርካሪው ሊብሬ እና ታርጋ ለመንገድ ትራንስፖርት በመመለሱ ወይም መድን ድርጅት ቅሪት አካለን በመረከቡ ምክንያት ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት የስራ ክፍል**

- የታክስ ከፋዮች ምዝገባና አገልግሎት የስራ ሂደት/ቡድን

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልናለ

**ለ) ድርጅት ለመዝጋት፣ ባለቤትነት ለማዛወር፣የስም ወይም የአድራሻ ለውጥ ለማድረግ፤ አክሲዮን ለማስተላለፍ የሚጠየቅ የምስክር ወረቀት (ክሊራንስ)፤**

**አገልገሎቱን ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች**

- ድርጅትን ሙለ በሙለ ለመዝጋት፣ ከድርጅቱ ንብረት ከ50% በላይ ለመሸጥ፣ የአክስዮን/ንብረት ዝውውር ለማድረግ፣ የስም ለውጥ ለማድረግ፤ ሥራ ላልጀመረ ፈቃድ ለመመለስ፣ ከአንዴ በላይ ድርጅቶች ለመዋሃድ የኦዲት ወይም የታክስ አወሳሰን ውሳኔ፤
- ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ነፃ ስለመሆን ማስረጃ ማቅረብ (ድርጅት ለመዝጋት ብቻ)፤
- በሰነዶች ማረጋገቻና ምዝገባ አገልግሎት የፀደቀ የባለአክስዮኖች ቃለ-ጉባኤ፣ (ድርጅትን ለመዝጋት ብቻ)፤
- የቋሚ ንብርት ዝርዝር የመዝገብ ዋጋ እና ኦሪጅናል ሊብሬ/ካርታ ኮፒ ማቅረብ (ባለቤትነት ለማዛወር)፤
- ድርጅት ለመዝጋት ወይም የንግድ ፈቃድ ለመመለስ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት የጠየቀ ግብር ከፋይ አጠቃላይ ኦዲት ተደርጎ እንዲከፈል የተጠየቀውን ውዝፍ የታክስ ዕዳ እና ወቅታዊ የታክስ ክፍያ አስኪፈጸም ድረስ ሥራ አለመስራቱን በሦስተኛ ወገን የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ፤
- የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ለመሸጥ ወይም ሥም ለማዛወር ተጠይቆ ማሽነሪው ወይም ተሸከርካሪው ተበላሽቶ የቆመ ከሆነ ከቆመበት ጋራዥ፣ቀበላ አስተዳደር ወይም ይህንን ማረጋገጥ ከሚችል የመንግስት መ/ቤት የተሰጠ ማረጋገጫ ማቅረብ፤
- የንግድ ሥራ ፈቃድ አውጥተው የንግዴ ሥራ ያልሰሩ ታክስ ከፋዮች የንግድ ሥራ ፈቃድ ለመመለስ ጥያቄ ሲያቀርቡ ከታክስ ባለስልጣኑ የሥራ ክፍሎችና ከሦስተኛ ወገን የተሰጠ ማረጋገጫ ማቅረብ፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት የስራ ክፍል**

- የታክስ ከፋዮች ምዝገባና አገልግሎት የስራ ሂደት/ቡድን

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**ሐ) የወጪ መጋራት ክፍያ ክሊራንስ**

- ማንነትን የሚገልጽ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ/ ፓስፖርት/ ወይም መንጃ ፈቃድ፤
- ከሚሠራበት መ/ቤት ወይም ድርጅት የአገልግሎት ማስረጃ ማቅረብ፤
- የሚፈለግበት የወጪ መጋራት በክፍያ /በአገልግሎት/ አጠናቆ መክፈሉን ማረጋገጫ፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት የስራ ክፍል**

- የታክስ ከፋዮች ምዝገባና አገልግሎት የስራ ሂደት/ቡድን

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልናለ

**መ) ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ስለመከፈሉ ለተቀጣሪ የሚሰጥ ማስረጃ**

- ማንነትን የሚገልጽ የታደሰ የቀበሌ/የመስሪያ ቤት መታወቂያ /ፓስፖርት/ መንጃ ፈቃድ፤
- ከሚሠራበት መ/ቤት ወይም ድርጅት የአገለገለበት ዘመንና ከመቀጠር ባገኘው ገቢ ላይ ግብር ስለመከፈሉ ማስረጃ ማቅረብ፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት የስራ ክፍል**

- የታክስ ከፋዮች ምዝገባና አገልግሎት የስራ ሂደት/ቡድን

አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

## ማረሚያ

ሰሞኑን በተሰራጨው የ«ገቢያችን ህልውናችን» 14ኛ ዓመት ቁጥር 163 ዕትም ጋዜጣ ገጽ 4 «ለግንዛቤዎ» ዐምድ ላይ «የግብር ማስከፈያ መጣኔ» በሚል የወጣው ጽሑፍ ውስጥ የሠንጠረዥ «ሀ» ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ተብሎ የተቀመጠው መረጃ በታይፐ ስህተት የሰፈረ በመሆኑ ትክክለኛው መረጃ ቀጥሎ ያለው መሆኑን ከታላቅ ይቅርታ ጋር እንጠይቃለን፡፡

**ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ግብር የማስከፈያ ምጣኔዎች**

| ተ.ቁ | የሚገኝ የወር ገቢ በብር | ተከፋይ የገቢ ግብር በሙቶኛ | ተቀናሽ በብር |
|---|---|---|---|
| 1 | 0 - 600 | ነፃ | 0 |
| 2 | 601 — 1650 | 10 | 60 |
| 3 | 1651 - 3200 | 15 | 142.50 |
| 4 | 3,201 - 5,250 | 20 | 302.50 |
| 5 | 5,251 - 7,800 | 25 | 565 |
| 6 | 7,801 - 10,900 | 30 | 955 |
| 7 | 10,900 - በላይ | 35 | 1,500 |

# በየዓይነቱ

አዘጋጅ፡- እታገኝ አቦሰጥ





ወፎቹ በትናንሽ ካርቶኖች ውስጥ በዚህ መልክ ነበር የታሸጉት፤

## ቦርሳ ውስጥ የተገኙ 20 ወፎች

ቤልጂየማዊው ተጓዥ በፔሩ ዋና ከተማ በሚገኘው ሊማ አየር ማረፊያ በእጅ ሻንጣው 20 ወፎችን ደብቆ ከሃገር ሊወጣ ሲል በቁጥጥር ሥር ውሏል።

ሂዮጉ ኮኒንግስ የተባለው የ54 ዓመቱ ጎልማሳ ወፎቹን በትናንሽ ካርቶኖች ውስጥ ካደረገ በኋላ ወደ ማድሪድ ስፔን ወስዶ ለመሸጥ አስቦ ነበር። ወፎቹን የወሰዳቸው ጥበቃ ከሚደረግላቸው የላቲን አሜሪካ ብርቅዬ አእዋፋት መጠለያ ነው።

ወፎቹ በታሸጉበት ካርቶን ውስጥ በሕይወት ቢገኙም ለሰዓታት በመቆየታቸው ላባቸው መርገፉን እና ፈሳሽ ከውስጣቸው የመመናመን ምልክት ማሳየታቸውን ባለሥልጣናት አስታውቀዋል።

በቁጥጥር ሥር የዋለው ቤልጂየማዊ ‹‹አእዋፋትን በሕገ-ወጥ መንገድ ማዘዋወር›› በሚል ክስ ተመስርቶበት የአምስት ዓመት እስራት ተፈርዶበታል፡፡

እንደነዚህ ዓይነት ወፎቹ በፔሩ፣ በኢኳዶር እና በቦሊቪያ ጥቅጥቅ ደን ውስጥ ብቻ የሚገኙ ናቸው። ብርቅዬ የሆኑ አእዋፋት በብዛት በሚገኙባት በፔሩ ሕገ-ወጥ የዱር እንስሳት አዘዋዋሪዎች ስጋቷ ናቸው፡፡

## ብልሀት፤ ይበልጣል ከጉልበት!

አንድ አዛውንት ገበሬ በአስር ቤት ላለው ልጃቸው፣ “ውድ ልጄ፤ ዘንድሮ ድንች መትከል አልቻልም፡፡ ምክንያቱም፤ መስኩን በራሱ መቆፈር ስለማልችል እዚህ ብትሆን ትረዳኝ ነበር” ብለው ይጽፉለታል፡፡

ልጁ ከአስር ቤት መልሶ፣ ‹‹አባዬ፤ ሜዳውን ለመቆፈር እንኳን አቅም እንደሌለህ አውቃለሁ፡፡ መሬቱን እንዳታስቆፍር፡፡ ከማሳው የሚወጣውን ኩንታል ያክል ድንች እኔ እገዛልሃለሁ፡፡ ምክንያቱም የሰረቅኩትን ወርቅ ሁሉ የቀበርኩት እዚያ ነው›› በማለት ይጽፋል፡፡

ደብዳቤውን ለአባትየው ለመስጠት የተቀበለው ፖሊስ ደብዳቤውን ምስጢር ይኖረዋል ብሎ ሲያነበው እንደገመተው ሆኖ አገኘው፡፡ ስለዚህ፤ በማግስቱ ወርቁን ለመፈለግ ማሳውን ሙሉ በሙሉ አስቆፈረው፤ ነገር ግን ምንም ወርቅ አልተገኘም፡፡

በማግስቱ ይህን የሰማው ልጅ ከእስር ቤት ለአባቱ እንደገና በጻፈው ደብዳቤ፣ ‹‹አሁን ማሳው ስለተቆፈረ ድንችህን ትከል፤ እኔ እዚህ ሆኜ ማድረግ የምችለው ይሄን ብቻ ስለሆነ›› ነበር ያለው፡፡

## እንደ አናናስ፡-

ላመንከበት ቀጥ ብለህ ቁም፤
ለራስህ ደግሞ የክብር ዘውድ ይኑርህ፤
ውስጥህ ግን ጣፋጭ ይሁን!



## ንሥሮችን ተከታይ በሞባይል እዳ ውስጥ የተዘፈቁ አጥኚዎች



ከአገር አገር የሚሰደዱ ንሥሮችን እየተከተሉ የሚያጠኑ ሩሲያዊያን ሳይንቲስቶች ወደ ኢራንና ፓኪስታን ተጉዘው ገንዘባቸውን ከመጨረሳቸው በተጨማሪ በሞባይል የኢንተርኔት አገልግሎት ከፍተኛ እዳ ውስጥ ገብተዋል።

አጥኚዎቹን ለእዳ የዳረጓቸው ንሥሮች ከደቡባዊ ሩሲያና ከካዛኪስታን የተነሱ ሲሆኑ በተለይ ሚን ተብሎ የሚጠራው ንሥር ከካዛኪስታን ተነስቶ ወደ ኢራን ስለሚጓዝ እሱን መከተሉ ነው ለአጥኚዎቹ እዳ መናር ምክንያት የሆነው።

አጥኚዎቹ ከሚከታተሏቸው አእዋፋት ላይ የሚሰበስቡት አጭር የጽሑፍ መልዕክት እንዳሉበት አገር የክፍያ ተመን ሁኔታ የተለያየ በመሆኑ ንሥሮቹ በሚሄዱባቸው አገራት ብዛት ክፍያው ከፍ እያለ ይሄዳል።

ሳይንቲስቶቹ የዱር እንስሳት ጥበቃን በተመለከተ ጥናት የሚያደርግ ሩሲያ ውስጥ የሚገኝ የአንድ ማዕከል የበጎ ፈቃድ ተሳታፊዎች ናቸው።

አጥኚዎቹ የገቡበትን ችግር የተገነዘበው የሩሲያው የሞባይል ስልክ አገልግሎት አቅራቢ ሜጋፎን የተባለው ድርጅት እዳቸውን ሰርዞ ከዚህ በኋላ የሚጠቀሙትን የሞባይል ኢንተርኔት አገልግሎት በቅናሽ እንዲከፍሉ ወስኗል።

ሳይንቲስቶቹ የገቡበትን የስልክ ዕዳ ለመክፈል በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ያሉ ተከታዮቻቸው ገንዘብ እንዲለግሷቸው ጠይቀው ነበር።

አጥኚዎቹ በሞባይል የኢንተርኔት አገልግሎት እዳ ውስጥ መግባታቸውን ተከትሎ በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ላይ ድጋፍ ለማግኘት ባቀረቡት የድጋፍ ጥሪ መሰረት ከ1500 ዶላር በላይ ለመሰብሰብ ችለው ነበር።

ሳይንቲስቶቹ እዳ ውስጥ የከተታቸው ንሥሮቹ የት እንዳሉ በሚያመለከተው አጭር መልዕክት አማካይነት አእዋፋቱ ለደህንነታቸው አመቺ የሆነ ስፍራ መድረስ አለመድረሳቸውን በሳይንሳዊ መንገድ ለማወቅ ያስችላቸዋል።

ለየት ያለ የንሥር ዝርያ እንደሆኑ ከሚነገርላቸው ሚን ከተባሉት ንሥሮች መካከል አጥኚዎቹ 13ቱን በአሁኑ ጊዜ የት እንዳሉና ያሉበትን ሁኔታ እየተከታተሉ ሲሆን በዚህ ወቅት ከሚራቡበት የሳይቤሪያና የካዛኪስታን አካባቢዎች ወደ ደቡብ እስያ ይሄዳሉ።

የሞባይል ስልክ አገልግሎት አቅራቢው ሜጋፎን፤ የሳይንቲስቶቹን እዳ መሰረዙ የጀመሩትን ንሥሮቹን የመከታተል ሥራ እንዲቀጥሉ ከማስቻሉ በተጨማሪ ለደህንነታቸው የሚያስፈልግ በጣም ጠቃሚ መረጃን ለመሰብሰብ ያግዛል ተብሏል።

# ተስፋ የተጣለባቸው የጉምሩክ...

ከገጽ 8 የዞረ

፡ በ1985 ዓ.ም የዓለም ጉምሩኮች ድርጅትን የተጣጣመ የሸቀጦች አሰያየምና አመዳደብ ሥርዓትን በመፈረም እና በአዋጅ በማጽደቅ የጉምሩክ አሠራር በበለጠ ዘመናዊ እንዲሆን የሚያስችሉ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል፡፡

**የጉምሩክ ጣቢያዎች እና ዋና ዋና የንግድ መተሳሰፊያ መስመሮች**

በአክሱም እና በመካከለኛው ዘመኖች እንዲሁም ከመቶ ዓመት ወዲህ ያሉት የንግድ ማዕከላትና የንግድ መስመሮች በየጊዜው ተለዋውጠዋል፡፡ ይህንንም ተከትሎ የጉምሩክ መቆጣጠሪያ እና መቅረጫ ጣቢያዎች ተለዋውጠዋል፡፡ ከነዚህ ጣቢያዎች መካከል ሐረር፣ ድሬዳዋ እና ጋምቤላ ይገኙ የነበሩት ዋና ዋና የአገራችን የጉምሩክ ጣቢያዎች ነበሩ፡፡

ሐረር በዘይላና በበርበራ ወደቦች እና በመሐል አገር መካከል የምትገኝ የንግድ ማዕከልና የንግድ መተላለፊያ ከተማ ነበረች፡፡ አምስቱ የሐረር ከተማ በሮች የጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያ ሆነው በመተላለፍም ከቱርክ፣ ከግብጽ፣ ከፈረንሳይ፣ ከጣልያን እና ከእንግሊዝ ጋር የንግድ ልውውጥ ታደርግ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት የጉምሩክ ቀረጥ በዓይነት ብቻ ሳይሆን በገንዘብም ይከፈል ነበር፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ዓርማ ያላቸው የቀረጥ ቴምብሮች እንደ ጉምሩክ ዲክላሬሽን ያገለግሉ ነበር፡፡

ሐረር በማዕከላዊ የኢትዮጵያ መንግስት ቁጥጥር ሥር ከሆነች በኋላ የአዲስ አበባ ጂቡቲ የምድር ባቡር ግንባታ ድሬዳዋ ከተማ እስከደረሰበት ጊዜ ድረስ ዋናዋ የንግድ ማዕከልና የንግድ መተላለፊያ ከተማ ነበረች፡፡ ከሐረር ከጉምሩክ ቀረጥ የሚሰበሰበው ገቢም ከፍተኛ እና አስተማማኝ በመሆኑ የኢትዮጵያ መንግስት ከኢጣሊያን መንግሥት ለሚያገኘው የአራት ሚሊዮን ሊሬ ብድር እንደ ዋስትና ሆኖ አገልግሏል፡፡

የድሬዳዋ ከተማ አመሠራረት ከአዲስ አበባ ጂቡቲ የምድር ባቡር ዝርጋታ ጋር የተያያዘ ነው። በዚህ ወቅት ዕቃዎች ከጂቡቲ እስከ ድሬዳዋ ተጭነው፤ ከድሬዳዋ በኋላ በጭነት እንስሳት እየተጓጓዙ አዲስ አበባ ይደርሱ ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ ከተማዋ ለብዙ ዓመታት ዋናዋ የኢትዮጵያ ጉምሩክ የሚገኝባትና የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ የሚሰበሰብባት በከፍተኛ ፍጥነት እንድታድግ አግዟታል።



የጉምሩክ መኮንኖች ተመርቀው ወታደራዊ ትርዒት ሲያቀርቡ፤

የጋምቤላ ወደብና የንግድ ጣቢያ የምዕራብ ኢትዮጵያን ንግድ ለመቆጣጠርና አካባቢውን ወደ ሱዳን ለመሳብ የታሰበ ነው፡፡ በእ.ኤ.አ 1902 ስምምነት መሠረት በባሮ ወንዝ ላይ የሚገነባው ወደብና ንግድ ጣቢያ በኢታንግ አካባቢ እንደሚገነባ የተጠቀሰ ቢሆንም ቦታው ከኢትዮጵያ ደጋማ አካባቢ የሚርቅ በመሆኑ እ.ኤ.አ በ1904 ወደ ጋምቤላ እንዲዛወር ተደርጓል፡፡

**የተደራጀ የቁጥጥር ሥርዓትን ስማስፈን የተሠራው ሥራ**

በጉምሩክ ቁጥጥሩ እና በቀረጥ ማስከፈያ ጣቢያዎች የሚደረገው ቁጥጥር እና የአሠራር ሥርዓት በየጊዜው የነበሩ መንግሥታት ከፍተኛ ክትትል ሳይለየው ተካሒዷል፡፡ ሥራውንም ፊናንስ ፖሊስ፣ የአገር መከላከያ ሠራዊት፣ የፌደራል ፖሊስ እና ሌሎች የፀጥታ ኃይሎች ከሕብረተሰቡ ጋር በትብብር ይሠሩ ነበር፡፡

**ምረቃ**

ጉምሩክ ኮሚሽን የኮንትሮባንዲስቶችን እንቅስቃሴ ለመግታት ከግል ጥቅም ይልቅ አገር አስቀድመው ለሥራቸው እና ለአገራቸው በመታመን እስከ ሕይወት መስዋዕትነት ድረስ እየከፈሉ የሚገኙ ሠራተኞች አሉት፡፡

ኮሚሽኑ አሁንም የተጠናከሩ እና የተደራጁ የፍተሻ ጣቢያዎችን በማቋቋም የኮንትሮባንድ ዝውውርን ለመግታት ዋና ተግባሩን በመወጣት ላይ ነው፡፡ ለዚህም እንዲረዳ በሥነ-ምግባራቸው የታነፁ፣ በሰብዕናቸውም አርአያ የሚሆኑ፣ በእውቀታቸውና በክህሎታቸው የበቁ የቁጥጥር ባለሙያዎችን እያሰለጠነ ያሰማራል፡፡

ከዚህ አኳያ በቅርቡ ከመላው አገሪቱ የተውጣጡ 987 ወጣቶች ለ521 ሰዓታት በፖሊስ ሳይንስ፣ በጉምሩክ ደንብ ሕግና አሠራር እንዲሁም በአካል ብቃት ላይ ለሦስት ወራት ስልጠና ወስደዋል፡፡ በሲዳማ ክልል አፖስቶ በሚገኘው የደቡብ ፖሊስ ኮሌጅ ውስጥ ከሰለጠኑት መካከል 109ኙ ሴቶች ሲሆኑ ከመከላከያ ሰራዊት የተለያዩ ክፍሎች የተውጣጡ 39 አመራሮችም ተካፍለውበታል፡፡

በስልጠናው ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ሰልጣኞች ላፕቶፕ ኮምፒዩተር እና ሰርተፊኬት ከጉምሩክ ኮሚሽነር አቶ ደበሌ ቃበታ እና ከፌደራል ፖሊስ ምክትል ኮሚሽነር ጀነራል መላኩ ፋንታ ተበርክቶላቸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ በዚህ ጊዜም ተመራቂዎች ኮንትሮባንድን እና ሕገ-ወጥ ንግድን የመከላከል ከፍተኛ ኃላፊነት ስለተጣለባቸው ኃላፊነታቸውን በትጋት፣ በቅንነት እና በታታሪነት ተግባራዊ እንዲያደርጉ አሳስበዋል፡፡

በሥነ-ሥርዓቱ ላይ ማበረታቻ እንዲሁም ለስልጠናው ስኬት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላበረከቱ የዋንጫ እና ሰርተፊኬት ማበረታቻ ተሰጥቷል፡፡ ሰልጣኞችም ወደስራ ሲገቡ ህዝብ እና ሀገር የጣለባቸውን ኃላፊነት በታማኝነት እና በቅንነት እንዲሁም በጥሩ ስነ-ምግባር እንደሚወጡ በቃለ መሀላ አረጋግጠዋል፡፡

# የተበጠሰው የኮንትሮባንዱ ...

ከገጽ 8 የዞረ

መድረሻውን ለማጣራት እና የኮንትሮባንድ ዕቃውን ባለቤት ለመለየት ነው፡፡

በሌላ መልኩ የሥራ ሒደት አስተባባሪው ድርድሩን ባይቀበሉ እንኳ ሌሎች የተቋሙን ሠራተኞች በመመልመል ኮንትሮባንዱ ማለፉ የማይቀር በመሆኑ ጉዳዩን ለበላይ አመራር በማሳወቅ በጥልቀት ለመነጋገር የሥራ ሂደት አስተባባሪው ዋና ሳጅን አሜንን ወደ ቢሮ በመጥራት ውይይት አድርገዋል፡፡ በዚህም የሌብነት ሰንሰለቱንና በጉዳዩ የሚያገኘውን ጥቅም በመወያየት ስለሥራው አጠቃላይ ሁኔታ በሌላ ጊዜ እና ቦታ በመገናኘት እንደሚያወሩ በመቀጣጠር ተለያዩ፡፡

ጥር 2/2013 ዓ.ም. አዋሽ ሰባት ኪሎ አቢሲኒያ ሆቴል ዋና ሳጅኑ የሥራ ሂደት አስተባባሪውንና ኮንትሮባንዲስቱን አገናኛቸው፡፡ ኮንትሮባንዲስቱ ደሳለኝ በንግድ ሥራ የተሰማራ ሲሆን ከዚህ ቀደም የስርቆት ሰንሰለት በማዘጋጀት ዕቃ ሲያሳልፍ የነበረ ነው፡፡ ለአብነትም መስከረም 27/2013 ዓ.ም. ከምሽቱ 4፡00 ድንበር ተሻጋሪ በሆነ መኪና በሰሌዳ ቁጥር ኢት. 3-83764/24467 በዕለቱ በነበረ ፈታሽ ሁሴን መሀመድ አብዱ ተፈትሾ መኪናውን ባዶ በማስመሰል ሊያልፍ ሲሞክር በድንገተኛ ፍተሻ ተፈትሾ የ459ሺ ብር ዕቃ ተይዞበት ነበር፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ ሀሰተኛ የጉምሩክ ሰነድ በማዘጋጀት ሊያልፍ ሲሞክር ተደርሶበት ኬላውን በኃይል ጥሶ እንደሄደ እና ለዚህም የፌደራል ፖሊሶች ከለላ እንደሰጡት ለማስረዳት ሞክሯል፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ ሀሰተኛ የመንገድ ወረቀት በማዘጋጀት አምስት ጊዜ፤ ያለሰነድ ደግሞ 21 ጊዜ ማሳለፍ እንደቻለ አስረድቷል፡፡ ይህንን ሲሠራም ነባር የጉምሩክ ሠራተኛ እንዳለውና ፈቃደኛ ከሆነ ከአዲሱ ሰንሰለት ጋር እንደሚያስተዋውቀው በመግለጽ የሥራ ሂደት አስተባባሪውን ለማስረዳት ይሞክራል፡፡

ለአዲሱ የኮንትሮባንድ ሰንሰለት የፍተሻ ባለሙያው አቶ ሁሴን መሀመድና ምክትል ኢንስፔክተር አብዲ ሸይቼ አባላት መሆናቸውን ዋና ሳጅኑ ለአቶ ካሳሁን እምሩ የማስተዋወቅ ሥራ ሠርቷል፡፡ በዚህም መሰረት ኮንትሮባንዲስቱ በአንድ ኮንቴይነር 200ሺ ብር ሊከፍል የተስማማ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 50ሺ ለአቶ ካሳሁን እንዲሰጣቸው ተወስኗል፡፡

የኮንትሮባንድ ዕቃው ከመምጣቱ አንድ ቀን ቀደም ብሎ የካቲት 30/2013 ዓ.ም. በአዋሽ ሰባት ኪሎ ሩት ቪሌጅ በመገናኘት ባደረጉት ውይይት ዕቃው ከገዳማይቱ ተነስቶ በፍተሻ ባለሙያው ሁሴን መሀመድ አማካኝነት እንደተፈተሸ በማስመሰል አስፈላጊ መረጃ ሞልቶ እንዲለቀው ነው የተወጠነው፡፡ የፌደራል ፖሊስ የሻለቃው አስተዳደር ኢንስፔክተር አየለ ለማ የኮንትሮባንድ ሰንሰለት ዋና መልማይ እንደሆነ እና አቶ ደሳለኝ ገብረክርስቶስ ስለዕቃው ዝርዝር መረጃዎችን የካቲት 28/2013 ዓ.ም. ለአቶ ካሳሁን እምሩ እንዲያደርሳቸው ተደርጓል፡፡

መጋቢት 1/2013 ዓ.ም. ጠዋት 3፡00 አካባቢ በመሀመድ አብዱል ከሪም አሽከርካሪነት ዕቃው አዋሽ ኬላ የደረሰ ሲሆን በዕለቱ በነበረ ፈታሽ ሁሴን መሀመድ አማካኝነት ጭነቱን ሕጋዊ እንደሆነ በማስመሰል፣ ሀሰተኛ የትራንዚት ቁጥር በመሙላት እና ማህተም በመምታት እንዲለቀቅ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት አቶ ደሳለኝ መጋቢት 2/2013 ዓ.ም. ለሌብነት ሰንሰለቱ እንዲያከፋፍል 200ሺ ብር የሰጠው ሲሆን በዚህ ሰንሰለት የተሳተፉ ሰባት አባላት በመሆናቸው እኩል ሲካፈሉ 28ሺ 571.43 ብር እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ አቶ ሁሴን መሀመድም ከአቶ ካሳሁን እጅ 28ሺ 600 እንዲቀበል ተደርጓል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ አቶ ካሳሁንን ጨምሮ ሦስት የኮሚሽኑ ሠራተኞች በማኔጅመንቱ እውቅና መሰረት እየተወኑ በመሆናቸው ሌሎች የኦፕሬሽን ሥራዎች እስኪጠናቀቁ 91ሺ 685 ብር በካሽ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡

የመጀመሪያው ዙር እደተጠናቀቀ የፌደራል ፖሊስ አባሉ ሻለቃ ባልታወቀ ምክንያት ወደ አልበረከቴ የተዛዋሩ ቢሆንም ኢንስፔክተር አየለ ለማ ጥቅሙን ለማስከበር ከዋና ኮንትሮባንዲስቱ አቶ ደሳለኝ ጋር መጋቢት 22/2013 ዓ.ም በአዋሽ 7 ኪሎ ሩት ቪሌጅ በመገናኘት ከዚህ በፊት ያለፈውን የኮንትሮባንድ ዕቃ በተመለከተ ደካማና ጠንካራ ጎን ገምግመውና ሌሎች መረጃዎችን ተለዋውጠው ተለያዩ፡፡

መጋቢት 23/2013 ዓ.ም. ከቀኑ 8፡20 አካባቢ በኮንቴነር ቁጥር TGBU 2394830 እና TCKU 3400819 በተሽከርካሪ ኢት. 3-83764/24467 የማሽጊያ ቁጥር EU 17403036 ወደ አዋሽ መፈተሻ ኬላ ደርሷል፡፡ እንደተለመደው በፍተሻ ሠራተኛው ሁሴን መሀመድ አማካኝነት ጭነቱን ሕጋዊ በማስመሰል እና በዕለቱ በስሙ የተመዘገበውን ማህተም በመምታት ኬላውን እንዲያልፍ ተደረገ፡፡ ከዚያም እቃው በጉዞ ላይ እንዳለ ወደ 10፡20 ገደማ መተሀራ ከተማ ሕይወት ሆቴል ውስጥ ካሳሁን እምሩ፣ ኢንስፔክተር አየለ ለማ እና ደሳለኝ ገብረ ክርስቶስ በመገናኘት ተወያይተዋል፡፡ ምክትል ኢንስፔክተር አብዲ ሸይቼ እና ዋና ሳጅን አሜ ኢስማኤል ስለ ኮንትሮባንዱ ስለሚያውቁ አቶ ደሳለኝ ከ200ሺ በተጨማሪ 10ሺ እና ከዋናው 10ሺ ባጠቃላይ 20ሺ እንዲሰጥ ተስማምተዋል፡፡ በተጨማሪም ከኢንስፔክተር አየለ ለማ ጋር ለሚሠሩ ተጨማሪ ሰዎች 40ሺ ቢጠይቅም 35ሺ እንዲበቃው ተስማምተዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ በሰንሰለቱ የተካተቱ ሰዎችን እጅ ከፈንጅ ለመያዝ ከፌደራል ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ቢሮ የተውጣጣ ግብረ-ኃይል እንዲሁም የኮሚሽኑ ሠራተኞች በገንዘብ ክፍፍሉ ወቅት እንዲያዙ ለማድረግ እንቅስቃሴ ተደርጓል፡፡ በዚህ ወቅት የመተሃራ ፖሊስ አዛዥ ለዋና ኮንትሮባንዲስቱ ሽፋን በማድረግ በመርማሪ ፖሊሱ እና በኮሚሽኑ የኢንተለጀንስ ባለሙያ ላይ የግድያ ሙከራ ቢያደርግም በፌደራል ፖሊስ ግብረ-ኃይል በቁጥጥር ስር ውሏል፡፡ ዕቃውን የጫነው መኪናም በደረሰበት በሌላ ግብረ-ኃይል ክትትል ሲደረግበት ቆይቶ ከነሾፌሩ ተይዟል፡፡ የፍተሻ ባለሙያው ሁሴን እንደለመደው ከአቶ ካሳሁን እምሩ ሊቀበል አዋሽ ሩት ቪሌጅ ተገናኝተው ሲቀበል ለመያዝ ቢሞከርም ጊዜው ምሽት በመሆኑ ገንዘቡን እንደተቀበለ ሊያመልጥ ችሏል፡፡

ይህን ጉዳይ የተከታተለው የልደታ ምድብ ችሎት ወንጀለኞችን እንደየተሳትፏቸው ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

**ምንጭ ፡-** የጉምሩክ ኮሚሽን ኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት

# የጋና የስፖርት...

ከገጽ 8 የዞረ

ታስቦ የወጣ ነው መባሉን ኢትዮ ኤፍ ኤም 107.8 ሬዲዮ ዘግቧል፡፡

በሀገራችንም በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 57 መሠረት አንድ ሺ እና ከዚያ ብር በላይ የሆነ የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ጨዋታ ለአሸናፊ ከሚሰጥ ሽልማት ላይ 15 በመቶ የገቢ ግብር በባለፈቃዱ አማካይነት ተሰብስቦ በአስተዳደሩ በኩል ለገቢ ሰብሳቢው መ/ቤት ገቢ ማድረግ እንዳለበት ተሻሽሎ በወጣው የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 172/2013 ላይ ተቀምጧል፡፡

# Tips

By Shimelis Sisay

## The ministry has planned to collect 529.3 billion birr

Ministry of Revenue has a plan to modernize the tax administration system and enhance tax revenue. To achieve this goal the ministry is doing an activity of massive awareness creation, public education, and community engagement.

During the fiscal year of 2015, the ministry achieved great success in collecting revenue and controlling smuggling by collaborating with the institute that is accountable to the ministry that as the Ethiopian Customs Commission she added.

Although there have been encouraging achievements in the revenue sector, further work is required to enhance the national revenue and the ministry has developed the middle age plan (2016-2018) to achieve this goal.

By developing this, the ministry has planned to collect 529.3 billion in the fiscal year of 2016.

## The Northwest branch's daycare has begun operations

In the instance, Minister of Revenues Mrs. Aynalem Nigussie, said that the Ministry of Revenues is undertaking several positive initiatives to create a conducive environment for the employees. Among those, the establishment of daycare is the Ministry's top priority.

The daycare's establishment will positively impact enhancing productivity and securing the relative advantage of women and youth, according to the minister.

Mr. Tolu Fite, manager of the Northwest branch, said that 60 percent of the employees are women, and establishing this daycare is crucial to increasing the sector's productivity and verifying the relative advantage of the women and youth.



## Quotations

- Nothing is certain except for death and tax. (Benjamin Franklin)
- Power corrupts: absolute power corrupts absolutely. (John Dalberg Acton)
- The love of money is the root of all evil. (The Bible)
- The truth will set you free. (The Bible)
- Three can keep a secret if two of them are dead. (Benjamin Franklin)
- All that glitters is not gold. (William Shakespeare)
- There is no place like home. Dorothy (character)
- The only thing we have to fear is fear itself. (Franklin D. Roosevelt)
- Whatever you are, be a good one. (Abraham Lincoln)
- United we stand, divided we fall. (Aesop)

## "The Ministry is working together with stakeholders to provide online service."

- Ministry of Revenues

The Ministry of Revenues and the Ministry of Development and Planning held a discussion during which this was announced.

Mrs. Aynalem Nigussie, the minister of revenue, stated that the tax system is being made online and that, in the 2015 fiscal year, 93% of taxpayers reported their taxes online.

In practice this, contemporary database has been set up as her, and deploying this technology positively impacts making sincere decisions in the revenue sector.

Fitsum Asefa (Ph.D.), minister of planning and development on her side said that the revenue sector is one of the massive sectors that significantly contribute to the growth of the national economy.

According to her, much attention will be placed on leveraging various technologies to improve the sector's accessibility and provide the service that redeemed the era.



*Mrs. Aynalem Nigussie*



*Fitsum Asefa (Ph.D.)*

## About auditing

A. Services that need an audit to provide clearance
1. To sell or transfer more than fifty percent of business assets.
2. To close the organization partially or whole.
3. To change or reduce the business sector.
4. To transfer the commercial store to a third party by sale, gift, or inheritance.

B. Services that don't need an audit to provide clearance
1. To renew a business license or professional license.
2. To participate in the tender.
3. To carry out annual registration and examination (Claudio) for vehicles and construction machinery.
4. To acquire a Bank loan.
5. To obtain insurance compensation and change vehicle plate.
6. To change the organization name or address.
7. To reduce the business sector excluding the business wealth
8. To provide an approved document that includes the merged company's tax debt when companies are merged again;

# ሕገ-ግብር

አዘጋጅ:- ሰሎሞን ወርቁ

ይህ አምድ የታክስ አስተዳደርና የጉምሩክ አሠራር የሚመራበትን ህጐች፣ መመሪያዎችና አሰራሮች፣ ለሕግ ተገዢነት የሚያስተምሩ አስተሳሰቦችን፣ ሕጎችን ለአሠራር ምቹ የሚያደርጉና ፍትሃዊ የንግድ ውድድርን የሚያጎለብቱ አሰራሮችንና ተሞክሮዎችን የሚያስተዋውቅ ጽሑፍ ይቀርብበታል፡



ምልምል የጉምሩክ መኮንኖች፤

## ተስፋ የተጣለባቸው የጉምሩክ መኮንኖች

የግብፅ፣ የግሪክ፣ የሮም፣ የቻይና፣ የሕንድ ጥንታዊ መንግስታት እርስ በርሳቸውና ከሌሎችም አገራት ጋር ያደርጉት ለነበረው የንግድ እንቅስቃሴ የጉምሩክ መሥሪያ ቤት አቋቁመው ቀረጥ በመሰብሰብ ረገድ ከዓለማችን ቀዳሚ አገራት መሆናቸውን የታሪክ መዛግብት ያሳያሉ፡፡

ኢትዮጵያ ደግሞ ከተቀረው ዓለም ጋር የንግድ ልውውጥ ማድረግ ከጀመረችበት ከአክሱም ሥልጣኔ በፊት ከነበረው ጊዜ ጀምሮ ጉምሩክ እና የጉምሩክ አሠራር እንደነበረ «የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም» በሚል የተዘጋጀው ሰነድ ያመለክታል፡፡ በይበልጥ ግን እየተስፋፋ የመጣው ከአዲስ አበባ ጂቡቲ የምድር ባቡር ምስረታ በኋላ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የድሬዳዋ እና የአዲስ አበባ ዋና የጉምሩክ ጣቢያዎች ተመስርተዋል፡፡ ጣቢያዎቹ በወቅቱ ዋነኛ የመንግስት ገቢ ምንጭ የነበሩ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያን የጉምሩክ አሠራር ለማዘመን ከ1935 ዓ.ም. ጀምሮ ዘመናዊ አዋጆችን እና ደንቦችን በማውጣት አሠራሩ እንዲሻሻል ተደርጓል። ከሐምሌ 30/1965 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የዓለም ጉምሩኮች ድርጅት አባል ሆናለች፡

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## የጋና የስፖርት ተወራራጆች 10 በመቶ ታክስ እንዲከፍሉ ተወሰነ

ጋናውያን የስፖርት አወራራጆች ለተወራራጆች ከሚከፍሉት የገንዘብ ሽልማት 10 በመቶ ታክስ ቆርጠው ለመንግሥት ገቢ እንዲያደርጉ የጋና መንግሥት ውሳኔ አስተላለፈ፡፡

የጋና የገቢዎች ባለሥልጣን እንዳሳወቀው፤ በሃገሪቱ የሚገኙ ሁሉም የስፖርት አወራራጅ ድርጅቶች ለታክስ አከፋፈሉ እንዲያመች አሠራራቸውን ማሻሻል እና በየጊዜው የሚጠቀሙትን ሶፍትዌር ማዘመን አለባቸው ብሏል፡፡

በሀገሪቱ በርካታ ቁጥር ያላቸው የስፖርት አወራራጅ ድርጅቶች ያሉ ሲሆን ድርጅቶቹን ለመቆጣጠር ጥብቅ ሕግ እንደወጣም ተጠቅሷል፡፡ አብዛኞቹ የአወራራጅ ድርጅቶቹ ደንበኞች ሥራ አጥ በመሆናቸው ሕጉ በጋና ወጣቶች ዘንድ ትችት ቀርቦበታል፡፡ የሃገሪቱ ባለስልጣናት በበኩላቸው ሕጉ አወራራጅ ድርጅቶችን ለመቆጣጠር

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## የተበጠሰው የኮንትሮባንዱ ሰንሰለት


ታኅሣሥ 19/2013 ዓ.ም. ከቀኑ 4፡00 አካባቢ የፀረ-ኮንትሮባንድ ግብረ ኃይል አባል የሆነው ዋና ሳጅን አሜ እስማኤል ሙሳ በወቅቱ የአዋሽ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር የሥራ ሂደት አስተባባሪ ወደሆኑት ወደ አቶ ካሳሁን እምሩ ቢሮ ይገባል፡፡ ከዚያም በሌብነት ሰንሰለት የኮንትሮባንድ ዕቃ እንዲያሳልፍ የድርድር ጥያቄ ያቀርብለታል፡፡ ጉዳዩን ሊፈትነው ያመጣው ወይም ሕገ-ወጥነቱን በጋራ በመሥራት ጥቅሙን ለመካፈል እንደሆነ በመጠርጠር ለማጤን ጊዜ እንዲሰጠው ይጠይቀዋል፡፡

አቶ ካሳሁን ያጋጠማቸውን ነገር የቅርብ ኃላፊያቸው ለሆኑት ለሕግ ተገዥነት ምክትል ሥራ አስኪያጅ ለአቶ ዘላለም ከንፈ በመንገር የድርድር ጥያቄውን እንዲቀበሉ ተወሰነ፡፡ ምክንያቶቹም፤ የድርድር ጥያቄ ያቀረበው አካል ሰንሰለቱ እስከምን ድረስ እንደሆነ ለማወቅ እና የኮንትሮባንድ አሠራሩ በምን ዓይነት ሁኔታ ኬላውን እንደሚያልፍ ተገንዝቦ ትምህርት ለመውሰድ ነው፡ ፡ ሌላው ደግሞ የኮንትሮባንድ ዕቃው መነሻውንና

ወደ ገጽ 6 ዞሯል




በ8199 ነጻ የስልክ ጥሪ ማንኛውንም መረጃ እና ለጥያቄዎቻችሁ ምላሽ ስለሚገኝበት በመደወል እንድትጠቀሙ እናሳስባለን።




በታክስ እና በጉምሩክ ጉዳዮች ላይ መረጃ ለማግኘት 8199

### የገቢዎች ሚኒስቴር ራዕይ

በ2022 ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ተገንብቶ ሀገራዊ ወጪ በታክስ ገቢ ተሸፍኖ ማየት

### እ ሴ ቶ ች

1. አገልጋይነት (Customer centric)
2. ሙያዊ ብቃት (Professionalism)
3. በቡድን መሥራት (Team work)
4. መሰጠት (Dedication/commitment)
5. ታማኝነት (Loyality)